## ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የምግብ ክለሳ እና ጉዳቶቹ

የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 በግልፅ እንዳስቀመጠው "መከለስ" ማለት የአንድን ምርት ግዝፈት ወይም ክብደት ለመጨመር፣ ጥራቱን ወይም ጥንካሬውን ለመቀነስ ወይም ለመጨመር፣ እይታው የተሻለ ወይም የበለጠ እንዲሆን በማስመሰል ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ዓላማ ሲባል ባዕድ ነገር ወይም ይዘት መጨመር ወይም የምርቱን ይዘት በሌላ ንጥረ-ነገር መተካት ነው» ይላል።

ይህንን ብያኔ ይዘን የምግብ ክለሳ ምንነት ስናይ የምግብ ክለሳ ማለት ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት በሚቀርብ ምግብ ላይ ሌላ ባዕድ ነገር በመጨመር ወይም ይዘቱን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በሌላ ነገር በመተካት ወይም በተገቢው መንገድ በንጽሕና ባለመመረቱና ባለመያዙ ከባዕድ ነገር ጋር እንዲነካካ ማድረግ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በምግብ ክለሳ ጊዜ የምግቡን ጣዕም፣ ተፈጥሮዓዊ ይዘትና መጠኑን በመቀየር የምግቡን ጥራትና ደኅንነት በከፍተኛ ሁኔታ ለብልሽት ይዳርጋል። የምግብ መከለስ በግለሰቦችም ሆነ በማኅበረሰብ ጤና ላይ ዘርፈ ብዙ የጤና ጉዳቶችን ያስከትላል፡፡

የምግብ ክለሳ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል ሲሆን ያልተገባ ጥቅም ለማካበት በማሰብ፣ በቸልተኝነት ወይም በማምረት፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝና ለሽያጭ በማቅረብ ሂደት ተገቢውን የጥራትና ደህንነት ጥንቃቄ ባለማድረግ ሊከሰት ይችላል። ይህንን ተከትሎም ተጠቃሚው ኅብረተሰብ ለመታለል፣ ለመጭበርበር ወይም ለጤና እክል ሊዳርግ ይችላል።

### ታስቦበት የሚደረግ ክለሳ

ይህ ዓይነቱ የክለሳ ሂደት የሚከሰተው አምራቾች ወይም ነጋዴዎች ሆን ብለው (Intentionally/Deliberately) ተጨማሪ ትርፍ ለማግኘት፣ ያላግባብ ለመበልፀግ፣ ክብደቱንና ይዘቱን ለመጨመር፣ ዝቅተኛ ዋጋዎችን በማሳየት የንግድ ገቢን ለማሳደግ፣ የኅብረተሰቡ የመግዛት አቅም ሲቀንስ/ሲጨምር፣ በዝቅተኛ ዋጋ የገበያውን ውድድር ለማሸነፍና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። ይህ አምራቾች ወይም ነጋዴዎች ትርፋማነትን ለማሳደግ በአቋራጭ ለመክበር ሲባል አፍቃሬ ነዋይ ያለባቸው፣ ተዓማኒነት የጎደላቸው የሚያደርጉት ድርጊት ነው። ሰብዓዊነትን ወደ ጎን በመተውና ገንዘብን የሚያስቀድሙ ናቸው፡፡

ለዚህ ዓላማቸውም በተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ምርቶች ውስጥ እንደዱቄት፣ ውሃ፣ ስኳር፣ ሙዝ፣ የአትክልት ዘይት፣ አፈር፣ የጠመኔ ዱቄት፣ ሞላሰስ፣ ተቆልቶ የተፈጨ የገብስ ዱቄት የመሳሰሉት ሌላ ባዕድ የሆኑ ነገሮችን ደባልቆ የመከለስ ተግባር እንዲሁም ምግቦች ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ ንጥረ ምግቦችን /Nutrients-Food/ በማስወገድ የሚፈፅምበት በመሆኑ ሆን ተብሎ ከማይፈፀም ክለሳ /Adulteration/ እጅግ አስከፊው ያደርገዋል፡፡

### በቸልተኝነት የሚደረግ ክለሳ

ይህ ዓይነቱ ክለሳ የሚከሰተው አምራቾች ወይም ነጋዴዎች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ብለው በሚያደርጉት ጥረት ሳይሆን ምርትን አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ሂደት ውስጥ መደረግ በሚኖርበት ጥንቃቄ ላይ ጉድለት መኖር ነው። በማምረት፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ ለሽያጭ በማቅረብ ሂደት የሚፈጠር ነው፡፡

በሀገራችን እንደየአካባቢው ሁኔታ የተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ምርቶችና መጠጦች ለባዕድ ነገር ክለሳ /Adultera-tion/ የተጋለጡ ናቸው። በአሁን ጊዜ እንደ ማር፣ ቅቤ፣ ወተትና የወተት ውጤቶች፣ ጤፍ፣ ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ በርበሬና እንጀራ ምርቶች ላይ እምነት አሳድሮ መገብየት የማይቻልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡

### የምግብ ክለሳ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

ቀዳሚው በአንድ ሀገር ላይ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ውድቀት የሚያስከትል ሲሆን በመቀጠልም የሚጨመሩ ባዕድ ነገሮች ምግቡን በመመረዝ ወይም አጠቃላይ የምግቡን ይዘትና መጠን ለብልሽት በማጋለጥ የሰው ልጅ በሚመገብበት ወቅት ከፍተኛ የጤና መታወክ ያስከትላሉ። ካንሰር፣ አላርጂክ፣ ተቅማጥ፣ አስም ለመሳሰሉ ከባድ በሽታዎች ያጋልጣሉ፡፡

የንግድ እንቅስቃሴ ማደግን ተከትሎ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ አንዳንድ ምርቶች ምንጫቸው ያልታወቀ፣ ከባዕድ ነገር ጋር የተደባለቁ እንዲሁም የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ጤናና ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ የምግብ ምርቶች ላይ ስለሚደረግ ባዕድ ነገር ክለሳ /Food adulteration/ የክለሳ ዓይነቶችና በሸማቹ ኅብረተሰብ ላይ ሊያስከትላቸው ስለሚችለው ተያያዥ ችግሮች ተመጋቢው ኅብረተሰብ እንዲገነዘበው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### በአብዛኛው ጊዜ ክለሳ የሚደረግባቸው

በአብዛኛው ጊዜ ክለሳ የሚደረግባቸው ምግቦች ወተት፣ ስኳርና ጨው፣ በርበሬ፣ ሽሮ ዱቄት (የአተር ወይም የባቄላ)፣ ማር፣ የጤፍ ዱቄትና የመሳሰሉት ናቸው። በብዛት የሚጨመሩት ባዕድ ነገሮችም ፡-ስታርች፣ የዱቄት ወተት፣ የሬሳ ማድረቂያ፣ የተለያዩ አንቲባዮቲክስ ፣ሳሙና፣ ቾክ፣ ነጭ አሸዋ፣ የተፈጨ ቀይ ድንጋይ፣ እርድ፣ ኖራ፣ ያልተፈቀዱ ቀለሞች ለማቅለሚያ፣ ጎመን ዘር፣ ጨዉው በብዛት፣ ስኳር፣ ሞላሰስ (የስኳር ተረፈ ምርት) እና የመሳሰሉት ናቸው።

እነዚህ ባዕድ ነገሮች በጤና ላይ የሚያስከትሉት ጉዳቶች፡
- ሞት፣ የነርቭ ችግር፣ ካንሰር/የኩላሊት ድካም፣ የሆድ ሕመም፣ ላልተፈለገ ወፍረት፣ ለስኳር ሕመም፣ የአይንና የነርቭ ጉዳት፣ ለጉበት መድከም፣ የጨጓራ ሕመምና ቁስለት፣ ደም የቀላቀለ ተቅማጥ፣ የመገጣጠሚያ ሕመም፣ የልብ ሕመም፣ የምግብ መመረዝ፣ የደም ሥርዓት መዛባትና የመቅኔ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል።

እነዚህ ባዕድ ነገሮች የሚጨመርባቸው ቦታዎች ደግሞ በመኖሪያ ቤት፣ በወፍጮ ቤቶችና በሌሎች ቦታዎችም ሊሆን ይችላል። በሀገራችንም ብሎም በአካባቢያችን በበዓል ወቅቶች በብዛት ሊከሰት የሚችል ድርጊትም ነው፡፡

መንግሥት ኅብረተሰቡን በምግብ ደኅንነት ከሚከሰቱ የምግብ ወለድ በሽታዎችና ሌሎች በምግብ ብክለት ከሚከሰቱ ችግሮች ለመከላከል በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 ለኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣንና ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት ኃላፊነት የሰጣቸው ሲሆን ለሰው ጤናና ደኅንነት አደገኛ የሆነ፣ ምንጩ ያልታወቀ፣ የጥራት ደረጃው የወረደ፣ ወይም የተመረዘ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈ ወይም ከባዕድ ነገሮች ጋር የተደባለቀ የንግድ ዕቃን ወይም ለሽያጭ ማቅረብ ወይም መሸጥ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር መሆኑን በንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ተደንግጓል::

በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 6 ለአስፈጻሚ አካል በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት አስተዳደር ባለሥልጣንንና የክልል የጤና ግብዓቶች ተቆጣጣሪ አካላት ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት በመከለሱ ወይም በሌላ ሕገ-ወጥ ድርጊት ምክንያት ሞት፣ ሕመም፣ የአካል ጉዳት፣ የጤና መታወክ ወይም ሌላ የጤና ችግር ያስከተለ ምርትን ወይም ይዘትን ይለያል፣ በናሙናው ላይ ጥናት ያደርጋል፣ ውጤቱን መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

በመሆኑም ሸማቹ ምርቶቹን ሲገዛ ከተለምዶው የተለዩ መጥፎ ባሕሪያትን የሚያሳይ ከሆነ ምግቡን ከመጠቀም መቆጠብ በተለይም ምግቦቹ የጣዕም፣ የይዘት፣ የመጠንና የሽታ ልዩነት ካላቸው፤ የምግብ ክለሳ ችግሮች ሲያጋጥሙ/ ሲከሰቱ ወይም እንደዚህ አይነት መሰል ጥርጣሬዎች ሲኖርዎት ለኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ወይም ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት ጥቆማ በማቅረብ የዜግነት ድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

**Tel : +251-11-552-41-22**
**+251-11-552-41-22**
**P.o.box. 5681**
**Free call. 8482**
**http://www.fmhaca.gov.et/contact/**
**E-mail contactefda@efda.gov.et**
**Telegram channel link**
**https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/**